17ዐሥረኛው ለሰሜኢ፣ ወጣ፤ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
18ዐሥራ አንደኛው ለዓዛርኤል፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
19ዐሥራ ሁለተኛው ለሐሻብያ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
20ዐሥራ ሦስተኛው ለሱባኤል፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
21ዐሥራ አራተኛው ለመቲትያ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
22ዐሥራ አምስተኛው ለኢያሪሙት፣ ለወ
ንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
23ዐሥራ ስድስተኛው ለሐናንያ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
24ዐሥራ ሰባተኛው ለዮሽብቃሻ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
25ዐሥራ ስምንተኛው ለሐናኒ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
26ዐሥራ ዘጠነኛው ለመሎቲ፣ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘምዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
27ሃያኛው ለኤልያታ፣ ለወንዶች ልጆቹና
ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
28ሃያ አንደኛው ለሆቲር፣ ለወንዶች ልጆ
ቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
29ሃያ ሁለተኛው ለጊዶልቲ፣ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
30ሃያ ሦስተኛው ለመሐዝዮት፣ ለወን
ዶች ልጆቹ ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
31ሃያ አራተኛው ለሮማንቲዔዘር፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12

## የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች

26 የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች
አመዳደብ፤

ከቆሬያውያን ወገን፤ ከአሳፍ ወንዶች
ልጆች አንዱ የሆነው የቆሬ ወንድ ልጅ
ሜሱላም።
2ሜሱላም ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
የመጀመሪያው ዘካሪያስ፣
ሁለተኛው ይዲኤል፣
ሦስተኛው ዮዛባት፣
አራተኛው የትኒኤል፣
3አምስተኛው ኤላም፣
ስድስተኛው ይሆሐናን፣
ሰባተኛው ኤሊሆዔናይ።
4ዖቤድኤዶምም እንደዚሁ ወንዶች
ልጆች ነበሩት፤
የመጀመሪያው ሸማያ፣
ሁለተኛው ዮዛባት፣
ሦስተኛው ኢዮአስ፣
አራተኛው ሣካር፣
አምስተኛው ናትናኤል፣
5ስድስተኛው ዓሚኤል፣
ሰባተኛው ይሳኮር፣
ስምንተኛው ፒላቲ፤
እግዚአብሔር ዖቤድኤዶምን ባርኮታልና።
6እንዲሁም ልጁ ሸማያ ወንዶች ልጆች
ነበሩት፤ እነርሱም በቂ ችሎታ ስለ
ነበራቸው የአባታቸው ቤት መሪዎች
ሆነው ነበር። 7የሸማያ ወንዶች ልጆች፤
ዖትኒ፣ ራፋኤል፣ ዖቤድ፣ ኤልዛባድ፤
ዘመዶቹ ኤሊሁና ሰማክያም እንደዚሁ
በቂ ችሎታ ነበራቸው። 8እነዚህ ሁሉ
የዖቤድኤዶም ዘሮች ሲሆኑ፣ እነር
ሱም ሆኑ ወንዶች ልጆቻቸውና ቤተ
ዘመዶቻቸው ሥራውን ለመሥራት
በቂ ችሎታ ነበራቸው። የዖቤድኤ
ዶም ዘሮች ባጠቃላይ ሥልሳ ሁለት
ነበሩ።
9ሜሱላም በቂ ችሎታ ያላቸው ወንዶች
ልጆችና ቤተ ዘመዶች ነበሩት፤ ቍጥ
ራቸውም ባጠቃላይ ዐሥራ ስምንት
ነበረ።
10ከሜራሪ ወገን የሆነው ሖሳ ወንዶች
ልጆች ነበሩት፤ የመጀመሪያው ሽምሪ
ነበረ፤ የበኵር ልጅ ባይሆንም እንኳ፣
አባቱ ቀዳሚ አድርጎት ነበር። 11ሁለ
ተኛው ኬልቅያስ፣ ሦስተኛው ጥበ
ልያ፣ አራተኛው ዘካርያስ፤ የሖሳ ወን
ዶች ልጆችና ቤተ ዘመዶቹ ባጠቃ
ላይ ዐሥራ ሦስት ነበሩ።
12የቤተ መቅደሱም ጠባቂዎች በአለቆቻ
ቸው ሥር ተመድበው ልክ እንደ ቤተ
ዘመዶቻቸው ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ቤተ
መቅደስ ሥራ ለማከናወን ምድብ ተራ
ነበራቸው። 13ለእያንዳንዱም በር ወጣት
ሽማግሌ ሳይባል ለሁሉም እኩል ዕጣ
ተጣለ።
14የምሥራቁ በር ዕጣ ለሴሌምያ ወጣ።
ከዚያም ምክር ዐዋቂ ለሆነው ለልጁ ለዘ
ካርያስ ዕጣ ጣሉ፤ እርሱም የሰሜኑ በር

25፥31 1ዜና9፥33
26፥1 1ዜና9፥17
26፥2 1ዜና9፥21
26፥5 2ሳሙ6፥10፤ 1ዜና13፥13፤16፥38
26፥10 ዘጸ21፥16፤ 1ዜና5፥1
26፥12 1ዜና9፥22
26፥13 1ዜና24፥5
26፥14 1ዜና9፥18፡ 21

